የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

# በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተመዝግበው የሚገኙ የሀገር ዐቀፍና የክልል ፓርቲዎች (በዐዋጅ ቁ. 1162/2011 መሠረት) ማሟላት ያለባቸውን ግዴታዎች ለማስፈፀም የወጣ መመርያ ቁ 3/2012

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ሥነ ምግባር ዐዋጅ ቁ.1162/2011 አንቀጽ 160 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ዐዋጁ ከመውጣቱ በፊት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዐዋጁ የተቀመጡትን መሥፈርቶች ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ማሟላት ያለበት መሆኑን ይደነግጋል። ይህንን የዐዋጁን ድንጋጌ ለማስፈጸም ቦርዱ ይህንን መመርያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመርያ “ሀገር ዐቀፍና የክልል ፓርቲዎች ማሟላት ያለባቸውን ግዴታ ለማስፈጸም የወጣ መመርያ ቁ. 3/2012” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመርያ ውስጥ፤

1. “ዐዋጅ” ማለት የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ እና የምርጫ ስነ ምግባር ዐዋጅ ቁ. 1162/2011 ነው።
2. “ቦርድ” ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው።
3. “ክልል” ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል።

## ክፍል ሁለት
## የፖለቲካ ፓርቲዎች ማሟላት ያሉባቸው ግዴታዎች

### 3. የአገር አቀፍ ፓርቲ መስራች አባላት ብዛት

1) በአዋጁ አንቀጽ 64 በተደነገገው መሰረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ የሚመሰረተው ቢያንስ 10,000 መሥራች አባላት ሲኖሩት እና ይህንን የሚያረጋጥ የአባላቶቹን ፊርማ የያዘ ማረጋገጫ ሰነድ ሲያቀርብ ነው።

በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ከተመለከቱት መስራች አባላት ውስጥ የአንድ ክልል ነዋሪዎች ከ40 በመቶ (ማለትም ከአራት ሺህ) መብለጥ የለባቸውም። የተቀሩት መሥራች አባላት ነዋሪነታቸው ከሌሎች ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሆነው በእያንዳዱ ክልል መደበኛ ነዋሪ የሆኑት ደግሞ ከ15 በመቶ የማያንሱ መሆን አለባቸው።

2) ከላይ በተመለከተው መሰረት ከቀረቡት የመስራች አባላት ዝርዝር እና ፊርማ ውጪ ያሉትን የመስራች አባላቱን ክልላዊ ስብጥር የመወሰን ስልጣን ፓርቲው አለው።

3) ከአዋጁ መውጣት በፊት የተመዘገበ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የመስራች አባላት ቁጥር ፓርቲው ቀደም ሲል በሚመዘገብበት ጊዜ አሟልቶ የተመዘገበ ከሆነ በድጋሚ እንዲያቀርብ አይጠየቅም። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ቦርዱ ለፓርቲው ማረጋገጫ ይሰጠዋል።

4) ከአዋጁ መውጣት በፊት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን የመስራች አባላት ቁጥር በሚመዘገብበት ጊዜ ያላቀረበ በሚሆንበት ጊዜ ፓርቲው ይህን የሚያሟላው ቀደም ሲል ለቦርዱ አቅርቦ ተመዝግቦበት በነበረው የአባላት ፊርማ ቁጥር ላይ በመጨመር ይሆናል።

5) የፖለቲካ ፓርቲው በአዋጁና በዚህ መመርያ መሰረት አባላትን በሚያሰባስብበት ጊዜ ሂደቱ የተሳካ እንዲሆን ቦርዱ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል።ጉዳዩ የሚመለከታቸው የአስተዳደር እና የህግ አስፈጻሚ አካላትም ተገቢውን እገዛ እንዳደረጉ ያረጋግጣል።

6) በቀጣይ የፓርቲው የስራ ዘመናት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ዝቅተኛው ክልላዊ የአባላት ስርጭት እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድ ፓርቲ ከፍተኛው የአባላት ቁጥር የሚገኝበት ክልል ሊቀያየር ይችላል።

7) አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁ መሰረት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ካሟላበት ጊዜ ጀምሮ ከተመለከተው የአባላት ቁጥር ያነሰ አባላት ሊኖሩት አይገባም።

## 4. የአገር-አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ መስራች አባል መሆን ስለሚችሉ ሰዎች

1) የሀገር አቀፍ ፖለቲካ ፓርቲ መስራች አባላት ሊሆኑ የሚችሉት ኢትዮጵያውያን እድሜያቸው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ

መብታቸው ያልተገፈፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆን በተሰጣቸው ማብራሪያ መሰረት መስማማታቸውን ከሙሉ ስማቸው ጎን ባኖሩት ፊርማቸው የገለፁና በተመዘገቡበት አካባቢ ነዋሪ ስለመሆናቸው ለፓርቲው የሰነድ ወይም የምስክር ማስረጃ ያቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡

2) በዚህ መመርያ አንቀጽ 3 እና በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተገለጹት የመሥራች አባላት መረጃ የአባሉን ሙሉ ስም፤ ፆታ፣ እድሜ፣ ቀበሌ ወይም ወረዳ፤ እንደ የአግባብነቱ የሚኖሩበትን ቦታ ልዩ ስም ወይም የቤት ቁጥር፣ የነዋሪነት የሰነድ ወይም ሌላ ማረጋገጫ ፣ የሰነድ ማረጋገጫ ያቀረበ ከሆነና ሰነዱ መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ መለያ ቁጥሩ፤ ፊርማ እና የምዝገባ ቀን የሚገልጽ እንዲሁም መረጃ ሰብሳቢው ስም፣ መረጃውን በትክክል ስለመሰብሰቡ በፊርማው ያረጋገጠበትን ሰነድ የያዘ መሆን አለበት፡፡

3) የፖለቲካ ፓርቲ የአባላት መዝገብ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱትን የመስራች አባላት መረጃዎች ለመመዝገብ የሚያስችል በቂ አምዶች እና "አስተያየት" የሚል ተጨማሪ አምድ ያለው መሆን አለበት፡፡

4) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የፓርቲዎች መስራች አባላትን የሚያሰባስበው ሰው አባል እንዲሆኑ ለሚጠይቃቸው ሰዎች ስለጉዳዩ በቂ ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡

5. ፓርቲው የሚያቀርበው የመስራች አባላት መረጃን ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ

1) በዚህ መመርያ ከአንቀጽ 3-4 የተመለከቱት የመስራች አባላት መረጃዎች ትክክለኛነት የሚረጋገጠው በፓርቲው ኃላፊዎች ወይም መሪዎች ወይም ፓርቲውን ለማስመዝገብ በሚያመለክተው ሰው ሲሆን የሚረጋገጠውም በሚያመለክተው ሰው ቃለ መሃላ ነው፡፡

2) አንድ ፓርቲ ተገቢውን የመስራች አባላት ቁጥር በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በቃለ መሃላ አስደግፎ ሲያቀርብ ቦርዱ የቀረበውን ሰነድ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለፓርቲው ተገቢውን ማረጋገጫ ይሰጠዋል፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥምና አጠራጣሪዎቹ መረጃዎች ቢቀነሱ ፓርቲው ሊኖረው ከሚገባው ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ያነሰ ሊኖረው ይችላል ብሎ ካመነ ቦርዱ የፓርቲው መስራች አባላት በሚኖሩበት አካባቢ የነዋሪነት ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣን ካለው አካል ጋር በመተባበር የመረጃዎቹን ትክክለኛነት ሊያጣራ ይችላል፡፡

**6. የመስራች አባላት የጾታና ማህበረሰባዊ ስብጥር**

በአዋጁ አንቀጽ 64(6) በተደነገገው መሰረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የመስራች አባላትን በሚያሰባስብበት ጊዜ የፆታን እና የተለያዩ በአካባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋጽኦ ባገናዘበ መልክ መሆን አለበት።

**7. የአባላት ቁጥርን በሚመለከት ለቦርዱ የሚቀርብ ሪፖርት**

አንድ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁና በዚህ መመርያ የተመለከተውን የአባላት ቁጥር ያለው ስለመሆኑ በየሁለት አመቱ የአባላት ዝርዝር ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት። በፓርቲው የሚቀርበው ሪፖርት የአባላቱ ቁጥር በአዋጁ ከተቀመጠው መጠን ያነሰ መሆኑን የሚያመለክት ከሆነ ቦርዱ የተጓደሉትን አባላት እንዲያሟላ ለፓርቲው ትዕዛዝ ይሰጣል።

**8. የክልል የፖለቲካ ፓርቲ መስራች አባላት ብዛት**

1) በአዋጁ አንቀጽ 65 በተደነገገው መሰረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ሆኖ የሚመሰረተው ቢያንስ 4,000 መሥራች አባላት ሲኖሩት ነው።

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀስ 1 ከተመለከቱት መስራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ (ማለትም ከሁለት ሺህ አራት መቶ) በላይ የሆኑት የክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች መሆን አለባቸው።

**9. ስለአገር-አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ የተነገሩት አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ስለመሆናቸው**

በዚህ መመርያ ከአንቀጽ 3 እስከ አንቀጽ 7 ስለአገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተመለከቱት መስፈርቶችና ግዴታዎች በክልል የፖለቲካ ፓርቲ ላይም በተመሳሳይነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**10. የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መሆን ስለማይችሉ ሰዎች**

1) በአዋጁ አንቀጽ 63 በተደነገገው መሰረት የሚከተሉት ሰዎች የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችሉም:-

ሀ) ዳኛ፤
ለ) ዓቃቤ ሕግ፤
ሐ) የመከላከያ ሰራዊት አባል፤ መ) የፖሊስ፣ የደህንነት እና የጸጥታ አካላት ሰራተኛ፤
ሠ) የቦርዱ ባለስልጣናት እና ሰራተኞች፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሱት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ ከፈለጉ የመንግሥት ስራቸውን መልቀቅ አለባቸው፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውን የጣሰ ሰው ከያዘው የመንግሥት ሥራ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ተቆጥሮ በሚመለከተው አካል አስፈላጊውን እርምጃ ይወሰዳል፡፡

4) በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት የፓርቲ መስራች አባላትን የሚያሰባስብ ሰው በዚህ አንቀጽ ከንኡስ አንቀጽ 1-3 ያሉትን ኃይለ ቃሎች ለሚያነጋግራቸው ሰዎች መግለጽ ይኖርበታል፡፡

## 11. የፖለቲካ ፓርቲ መስራቾች የፈረሙት ሰነድ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ

1) በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት በአገርአቀፍም ሆነ በክልል ፖለቲካ ፓርቲነት መሟላት የሚገባቸውን የአባላት ቁጥር ለማሟላት በአባላት የተፈረመው ሰነድ ለሕዝብ በይፋ የሚገለጽ ሰነድ ይሆናል፡፡

2) ቦርዱ የፓርቲ አባላቱ የፈረሙበትን ሰነድ ለህዝብ ይፋ ሲያደርግ የፓርቲዎች መስራች አባላትን የግል ህይወትና የግላዊነት መብት ባገናዘበ ሁኔታ የአባላቱን አድራሻ ሳይገልጽ ሊያቆይ ይችላል፡፡

## 12. በአዋጁ የተቀመጠውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር የማሟያ ጊዜ

1) ቀደም ሲል ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ የአባላቱ ቁጥር ከአስር ሺህ (10,000) ያነሰ ከሆነ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የአባላቱን ቁጥር ቢያንስ አስር ሺህ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት የአባላቱን ፊርማ ያሰባሰበበትን ሰነድ ለቦርዱ ማስረከብ አለበት፡፡

2) ቀደም ሲል ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ የክልል የፖለቲካ ፓርቲ የአባላቱ ቁጥር ከአራት ሺህ (4,000) ያነሰ ከሆነ ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን አንስቶ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ጠቅላላ የአባላቱን ቁጥር ቢያንስ አራት ሺህ ለማድረስ በአዋጁና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት አባላቱን ያሰባሰበበትን ሰነድ ለቦርዱ ማስረከብ አለበት፡፡

## 13. የፓርቲ ኃላፊዎችን አመራረጥ ስለማሳወቅ

በአዋጁ አንቀጽ 67(2)(ረ) በተደነገገው መሰረት የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የተመረጡ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው።

1) ቀደም ሲል ተመዝግቦ የነበረ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟላበትን የጊዜ ሁኔታ ቦርዱ የየፓርቲዎችን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ይወስናል።

**14. የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም**

1) በአዋጁ አንቀጽ 73 በተደነገገው መሰረት የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም የሚጸድቀውም ሆነ የሚሻሻለው በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ነው።

2) ቀደም ሲል ተመዝግቦ የነበረ የፖለቲካ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ በአዋጁ መሰረት ተሰብስቦ የፓርቲውን ፕሮግራም የሚያጸድቅበትን የጊዜ ሁኔታ ቦርዱ የፓርቲውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ይወስናል።

**15. የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይዘት**

በአዋጁ አንቀጽ 74 በተደነገገው መሰረት የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ማካተት አለበት።

1. የአባላት ቅበላ እና ስንብት ሁኔታ፤
2. የፖለቲካ ፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት፣ የሚመረጡበት ሥርዓት፣ የአገልግሎት ዘመናቸው እና የስራ ኃላፊነታቸውን፤
3. አባላት የሚከፍሉት የአባልነት መዋጮ ዓይነት፤
   የፖለቲካ ፓርቲው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት እንደሁኔታው በአዋጁና በዚህ መመርያ መሠረት አገር አቀፍ ፓርቲ ከሆነ ቢያንስ 500 አባላት፣ የክልል ፓርቲ ከሆነ ቢያንስ 200 አባላት በማድረግ የሚወስን ድንጋጌ፤
4. የፖለቲካ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት ዓመት አንድ ጊዜ መካሄድ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፣
5. የፓርቲው ቅርንጫፎች አወቃቀርና አሠራርን ጨምሮ የፓርቲውን መዋቅራዊ አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ፤
6. የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮችን ዝርዝር፤

7. የፖለቲካ ፓርቲው ከሌላ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውህደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የሚፈጥርበት፣ እንዲሁም ፓርቲው የሚፈርስበትን የውሳኔና የድርጊት ሂደቶች የያዙ ድንጋጌዎች፤
8. የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ አገራዊ ምርጫዎች እጩ ሆነው የሚቀርበበት ሥርዓት፣
9. የፖለቲካ ፓርቲው የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ እና የኦዲት አስተዳደር ሥርዓት አሰራር፣
10. የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ሥርዓት፣ የገቢ ማስገኛ አሰራር እና በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ስልጣን ያለውን አካል ወይም ኃላፊን የሚገልጽ ድንጋጌ፣
11. የፖለቲካ ፓርቲው የውስጥ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት፣
12. የፓርቲው አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልጽ፥ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጢር በሚሰጥ ድምጽ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን የሚገልጽ ድንጋጌ።

## 16. የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ አጸዳደቅ

አንድ ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ የፖለቲካ ፓርቲ እስካሁን ሲገለገልበት የነበረውን የመተዳደሪያ ደንብ በአዋጁ አንቀጽ 74 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 በተደነገገው መሰረት በማሟላት ቦርዱ በሚያስቀምጠው ጊዜ ውስጥ አጸድቆ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል።ደንቡን ለማሻሻል የጠቅላላ ጉባዔ የሚጠይቅ ከሆነ ፓርቲው በምን ያህል ጊዜ ይህንን መፈጸም እንደሚገባው የፓርቲውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መንገድ ቦርዱ ይወስናል።

## 17. የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ

1) ቀደም ሲል ተመዝግቦ በመንቀሳቀስ ላይ ያለ የፖለቲካ ፓርቲ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ ሳያካሄድ ጊዜው አልፎበት ከሆነ ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤውን ማካሄድ አለበት። ቦርዱ ይህንን በተመለከተ የፓርቲዎችን ማህደር በመመልከት ለፓርቲዎቹ ማሳሰቢያ ይልካል።

2) በደንባቸው መሰረት የጠቅላላ ጉባኤ ማካሄጃ ጊዜ ያላለፈባቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀደም ሲል ያደረጉት ጠቅላላ ጉባዔ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት ያልተሟላ ሆኖ ሲገኝ

ወይም ሌሎች የአዋጁን መስፈርቶችን ለማሟላት የጠቅላላ ጉባዔ የሚያስፈልግ ሲሆን ቦርዱ የፓርቲዎችን ነባራዊ ሁኔታ ፣የምርጫ ሰሌዳ እና የመሳሰሉትን ባገናዘበ መልኩ የጠቅላላ ጉባኤያቸውን ሊያደርጉ የሚገባበትን ጊዜ ወስኖ ያሳውቃቸዋል፡፡

## 18. የፓርቲ የኃላፊነት ቦታዎች

በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ለኃላፊነት ቦታ የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋጽኦን ያገናዘቡ መሆን አለባቸው፡፡ፓርቲው ይህንን አሳክቶ በማይገኝበት ጊዜ በዚህ ረገድ ያደረገውን በቂ ጥረት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 19. የፖለቲካ ፓርቲ ቅርንጫፎች ግንኙነት

አንድ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልልና ከክልል በታች ባሉ እርከኖች ቅርንጫፎች ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ በቅርንጫፎቹ መካከል ያለውን ግንኙነትና የስልጣን ተዋረድ በመተዳደርያ ደንቡ መደንገግ አለበት፡፡

## 20. ጠቅላላ ጉባኤ በወቅቱ አለማካሄድ የሚያስከትለው ውጤት

1) በአዋጁ አንቀጽ 98 በተደነገገው መሰረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በአዋጁና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ከሚገባው ጊዜ በሦስት ወር የዘገየ እንደሆነ ቦርዱ የፓርቲውን ተጨባጭ ሁኔታ ከግምት በማስገባት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉባኤውን እንዲያካሄድ ያሳውቀዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤውን ካላካሄደ ቦርዱ ፓርቲውን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ይወስዳል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 21. የመስፈርቶቹ ማሟያ የጊዜ ሰሌዳ

በአዋጁ አንቀጽ 160(3) እና በዚህ መመሪያ በተደነገገው መሰረት በአዋጁ በዚህ መመርያ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ያላሟላ ፓርቲ ቦርዱ ከምዝገባ እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፡፡

### 22. አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች ለመወከል ስለተቋቋሙ ፓርቲዎች

በዚህ መመሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝቅተኛ መስራች አባላትን እንዲሁም የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን በተመለከተ የተቀመጠው ግዴታ በፌዴሬሽን ምክር ቤት እውቅና የተሰጣቸውን አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም በይፋዊ የህዝብ ቆጠራ ውጤት ከ10,000-100,000 ብዛት እንዳላቸው የተረጋገጠ ማህበረሰቦች ለመወከል በሚል የተቋቋሙ ፓርቲዎች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

ይህን አላማ በመያዝ የተቋቋሙ ፓርቲዎችን የመስራች እና የጠቅላላ ጉባኤ ብዛት ቦርዱ ፓርቲዎቹ እንወክለዋለን የሚሉትን ህዝብ ቁጥር እና አሰፋፈር ከግንዛቤ በማስገባት ይወስናል፡፡

### 23. የተፈጻሚነት ጊዜ

ይህ መመርያ በቦርዱ ከፀደቀበት ከ ታህሳስ 26 ቀን 2012 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ብርቱካን ሚደቅሳ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ